# የመኢአድ ወጣቶች የግጥም ምሽት አካሄዱ።



የመላው ኢትዮጵያ አንድነት ድርጅት ወጣቶች በፓርቲው ዋና ጽሕፈት ቤት ቅጥር ግቢ ውስጥ በአዲስ ዘመን ዋዜማ ጳጉሜ 5 ቀን 2000 ዓ.ም የግጥም ምሽት ሥነ-ሥርዓት አካሄዱ።

በዚሁ የግጥም ምሽት ላይ በርካታ ወጣቶች በልዩ ልዩ ርዕሶች ቀስቃሽ፤ አስተማሪና አዝናኝ ግጥሞችን በሥፍራው ለተገኙ ታዳሚዎች አቅርበዋል። እንዲሁም የፓርቲው የኪነት ቡድን ሞረሽ ባንድ ልዩ ልዩ ጣዕመ-ዜማዎችን ያሰማ ሲሆን ጭውውትም በወጣቶች ቀርቧል።

የድርጅቱ የወጣቶች ክንፍ ባዘጋጀው የግጥም ምሽት ሥነ-ሥርዓት ላይ ክቡር ኢንጅነር ኃይሉ ሻውል የመላው ኢትዮጵያ አንድነት ድርጅት ፕሬዚዳንት በክብር እንግድነት ተገኝተው ባሰሙት ንግግር በወጣቶች ላይ ቀደም ሲል ከፍተኛ ሰቆቃ እንደደረሰባቸው በኀዘን አስታውሰው የወጣቶች ታጋይነትና የዓላማ ጽናት የሚለካው መከራን ታግሎ በማሸነፍ መሆኑን አስገንዝበዋል።

<<ከሕዝቡ ጋር ተሰልፈን እናሸንፋለን! ብለናል። አሁንም ሕዝባዊ ዓላማ ይዘናል። የኢትዮጵያ ሕዝብ ከኛ ጋር ነው። ስለዚህ በእርግጠኝነት እናሸንፋለን!>> ያሉት ክቡር ኢንጅነር ኃይሉ ሻውል አያይዘው ለወጣቶች በሰጡት መመሪያ <<ታሪካዊ ሂደት ላይ ናችሁ! ሕዝብ ከእናንተ የሚጠብቀውን በብቃት ተወጥታችሁ በተያያዝነው ሰላማዊ ትግል አካሄዳችሁን በበለጠ ታሪካዊ እንድታደርጉ ይሁን!>> ብለዋል።



ቀደም ሲል አቶ ማሙሸት አማረ የመላው ኢትዮጵያ አንድነት ድርጅት

EthioLion.com

ሥራ አስፈጻሚ ኰሚቴ አባልና የወጣቶች ጉዳይ ኃላፊ በበኩላቸው ባሰሙት ንግግር በሰላማዊ ትግል ሂደት እጅግ በጣም ብዙ መሰናክሎች እንደሚያጋጥሙ አስረድተው በመቀጠልም <<በሕገ-መንግሥቱ የተቀመጡት የመደራጀት፣ የመሰብሰብና የመጻፍ መብቶች ሁሉ የተከለከሉበት ሁኔታዎች መኖራቸውን ጠቅሰው የፓርቲያችንን ስም ለሌላ በመስጠት እና ተስፋ በማስቆረጥ ሰላማዊ ትግሉን እርም እንድንል የተወሰደብን እርምጃ ሌላው ትልቁ በደል ነበር>> ብለዋል።

አያይዘውም <<ነገን የምንናፍቅ ወጣቶች ነን። የብሩህ አዕምሮ ባለቤት ነን። ሮጦ የማይደክም ጉልበት አለን። አገራችን በእኛ ታብባለች። ከወደቀችበትም ትነሳለች። ተስፋ የቆረጠው ሕዝባችን በእኛ ትንሣኤን ያያል።>> ካሉ በኋላ በመቀጠልም ወጣቶች ከፍተኛ ኃላፊነት እንዳለባቸው ሲያስረዱ <<የዚች አገር እጣ ፋንታ በኛ በወጣቶች ጫንቃ ላይ ወድቋል። የአመራርነት ኃላፊነቱንም ተሸክመን የትግል ጉዞውን ወደፊት ለማራመድ ከመቼውም በበለጠ ተዘጋጅተናል።>> በማለት ተናግረዋል።

በመጨረሻም ወጣቶች የትግል ቁርጠኝነታቸውን የሚያረጋግጥ ባለ 8 ነጥብ የአቋም መግለጫ አውጥተዋል።

በዕለቱ በተካሄደው የግጥም ምሽት ዝግጅት ላይ 300 የሚደርሱ ታዳሚዎች የተገኙ ሲሆን ከነዚህ መካከል የፓርቲው የሥራ አስፈጻሚ ኰሚቴና የላዕላይ ምክር ቤት አባላትም መሳተፋቸው ታውቋል።







